# የታክስ አስተዳደራዊ እና የወንጀል ቅጣቶች

# እና

# ተያያዥ ጉዳዮች

ግንቦት 2014 ዓ.ም

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

# ይዘት

- ❑ ክፍል አንድ:- አጠቃላይ ሁኔታ
  - ዓላማ
  - ወሰን
  - ትርጓሜ
- ❑ ክፍል ሁለት:- ከታክስ ጋር በተገናኘ የሚፈጠር አለመግባባት
  - የግብር ከፋዩ መብትና ግዴታ

# ይዘት…

- በታክስ ውሳኔ አለመግባባት ሲፈጠር በየደረጃው አቤቱታ የሚቀርብበት ሂደት
- የታክስ ሕጎችን አስቀድሞ መተርጎም
- ለታክስ ወኪሎች ፈቃድ ስለመስጠት

❑ ክፍል ሶስት፡- የታክስ አስተዳደር እና የወንጀል ቅጣቶች እንዲሁም ሽልማቶች

- ማጠቃለያ
- ማጣቀሻ

# 1.1. ዓላማ

## ❑ ዋና ዓላማ

➢ በታክስ አስተዳደር ሕጉ በመወያየት በሕጉ የተቀመጡ መብትና ግዴታዎችን እንዲሁም አለመግባባት ሲፈጠር ምን ምን መደረግ እናዳለበት በመለየት በታክስ ለሚፈጸሙ ቅጣቶች እንዲሁም ሽልማቶችን ይገልጻሉ።

## ❑ ዝርዝር ዓላማ

✓ የታክስ ከፋዩን መብት እና ግዴታ ይለያሉ፤

✓ በታክስ ውሳኔ አለመግባባት ሲፈጠር በየደረጃው አቤቱታ የሚቀርብበትን ሂደት ይዘረዝራሉ፤

ዝርዝር ዓላማ...

- በታክስ የሚፈጸሙ የአስተዳደራዊ እና የወንጀል ቅጣቶች እንዲሁም ሽልማቶች ዙሪያ ገለጻ ማድረግ ይችላሉ፤
- አስተዳደራዊ ቅጣት በከፊል/ሙሉ በሙሉ የሚነሳባቸውን እና የማይነሳባቸውን ምክንያቶች ይዘረዝራሉ።

## 1.2. ወሰን

- **የሰነዱ ሽፋን፤** አዋጅ 983/2008፣ አስተዳደራዊ ቅጣት አወሳሰን መ.ቁ. 9/2011፣ የታክስ ወኪልት ፈቃድ አሰጣጥ መ.ቁ. 4/2011፣ የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት አሠራር መ.ቁ. 171/2013፣ የታክስ አስተዳደራዊ ቅጣት አነሳስ መ.ቁ. 137/2010ና 137/2010 መሻሻያ ናቸው።

ወሰን...

- **የሥልጠና ተሳታፊዎች**

- ሥልጠናው መሠረታዊ እንደመሆኑ ለግብር ከፋዩ እና በግብር ከፋዩ ድርጅት ለሚሠሩ በድርጅቱ ሠራተኝነታቸው የተረጋገጠላቸው ባለሙያዎች ይሰጣል፡፡

- **ጊዜ:-ሶስት ሰዓት/6፡00**

## 1.3. ትርጓሜ

- ይግባኝ ሊቀርብበት የሚችል ውሳኔ

- ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት

## ❑ ቅጣት

ቅጣት ማለት ስልጣን በተሰጠው አካል በአንድ ጉዳይ የተከሰሰውን ተከሳሽ ጥፋተኛ መሆኑን ካረጋገጡ በሆላ በአጥፊው ላይ ስርአትን ተከትለው የሚወስዱት የእርምት እርምጃ ነው፡፡

በታክስ ህጋችን ላይ ለግብር ከፋዩ በግልጽ የተቀመጡ መብት እና ግዴታወች ያሉ ሲሆን ግብር ከፋዩች በህጉ የተሰጣቸውን መብቶች ሲጠቀሙ በተመሳሳይ ሁኔታ ህጉ የጣለባቸውን ግዴታወችም የመወጣት ሀላፊነት ይኖርባቸዋል፡፡

የተጣለባቸውን ግዴታወች በማይወጡበት እና ጥፋቶችን በሚፈፅሙበት ጊዜ ለአስተዳደራዊ እና ወንጀል ቅጣቶች ይዳረጋሉ፡፡

## ትርጓሜ...

- ጽኑ ሕመም
- ባለሥልጣን
- ኮሚሽን
- የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት
- የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት ኃላፊ
- ቡድን
- የታክስ ወኪልነት የሙያ ፈቃድ

# ክፍል ሁለት

## የታክስ ህግ ተገዥነት እና ከታክስ ህግ ጋር በተገናኘ የሚፈጠር አለመግባባት

## 2.1. የታክስ ህግ ተገዥነት
### 2.1.1. ለታክስ ህግ ተገዥ መሆን

**ምን ማለት ነው?**

- ለታክስ ህግ ተገዥ መሆን ማለት **በታክስ ህጎች ላይ የተቀመጡ ግዴታዎችን በፈቃደኝነት ለመወጣት መስማማት/ፈቃደኛ** መሆን ማለት ነው።



**በምን ይገለፃል? (4ቱ መሰረታዊ የግብር ከፋዮች ግዴታዎች)**

- በግብር ከፋይነት መመዘገብ - **ትክክለኛ ምዝገባ**
- ታክስን **በወቅቱና በትክክል ማሳወቅ**
- **ትክክለኛ መረጃ** ለታክስ ሰብሳቢ ተቋሙ **ማቅረብ**
- ታክስን **በወቅቱና በትክክል በመክፈል**
  - **ሌሎች መገለጫዎች**
  - ትክክለኛውን መረጃ ለግብር ሰብሳቢው መ/ቤት ማሳወቅ
  - ለግብር አወሳሰን የሚረዱ የሂሳብ ሰነዶችን በአግባቡ መያዝ
  - የተቀመጡ የተመለሸ፣ ኪሳራ የማሳወቅ መብቶችን በአግባብ መጠቀም
  - ሌሎችም

## 2.1.2. ለታክስ ህግ ተገዥ አለመሆን

**ምን ማለት ነው?**

- ለታክስ ህግ ተገዥ አለመሆን ማለት **በታክስ ህጎች ላይ የተቀመጡ ግዴታዎችን ለመወጣት ፈቃደኛ አለመሆን** ማለት ነው፡፡

**በምን ይገለፃል? (4ቱ መሰረታዊ የግብር ከፋዮች ግዴታዎች ባለመወጣት)**

- በግብር ከፋይነት አለመመዝገብ
- ታክስን **በወቅቱና በትክክል አለማሳወቅ**
- **ትክክለኛ መረጃ** ለታክስ ሰብሳቢ ተቋሙ **አለማቅረብ**
- ታክስን **በወቅቱና በትክክል አለመክፈል**
  - ሌሎች መገለጫዎች
  - የተሳሳተ መግለጫ መስጠት (ገቢን ማሳነስ እና ወጪውን ማብዛት)
  - የማይገባውን ተመላሽ መጠየቅ፣
  - አላግባብ በተደጋጋሚ ኪሳራ ማሳወቅ
  - ደረሰኝ አለመቁረጥ
  - የሽያጭ መመዝገቢያን ማሽን በአግባብ አለመጠቀም
  - ሌሎችም



# 2.1.3. የህግ ተገዥነት ጠቀሜታ

**ለግብር ከፋዩ**

- የግብር መብታቸውን እና ግዴታቸውን በአግባቡ እንዲወጡ ይረዳል
- ከአላስፈላጊ ወጪ በማዳን ጊዜንና ገንዘብ ይቆጥባል /Tax Compliance Cost/
- መስተንግዶን ያቀላጥፋል
- መልካም ስምን ያተርፋል
- እና ሌሎችም

**ለመንግስት / ለሚኒስቴሩ**

- የሚጠበቀውን ገቢ በአግባቡ በመሰብሰብ የሀገርን ወጪ በሀገር ገቢ ለመሸፈን ያስችላል
- የተቀላጠፈ አገልግሎት ለመስጠት ይረዳል
- ለህግ ማስከበር እና ታክስን ለመሰብሰብ የሚወጡ ወጪዎችን ይቀንሳል /Tax Administration Cost/
- ትኩረትን ለህግ ተገዥ ባልሆኑት ለይ ለማተኮር ይረዳል
- እና ሌሎችም

## 2.2. የግብር ከፋዩ መብትና ግዴታ

- **መብት**
  - መረጃ የመጠየቅና ምላሽ የማግኘት እንዲሁም አስተያየት የመስጠት፣
  - በተገቢው ሁኔታ አገልግሎት የማግኘት እና ቅሬታ የማቅረብ፣
  - በክብር የመስተናገድና ለጥያቄዎች ምላሽ የማግኘት፣
  - በሂደት ላይ ያለ ጉዳይ የት እንደሚገኝ ጠይቆ የመረዳት፡፡
- **ግዴታ፤**
  - በግብር ከፋይነት የመመዝገብ፣
  - በሚኒስቴሩ የተፈቀደ ደረሰኝ የማሳተምና የመጠቀም፣

- ተገቢነት ያላቸው ሰነዶች የመያዝ፣
- በሕግ በተመለከተው ጊዜ ገቢውን ወይም ሽያጩን አሳውቆ ትክክለኛ ግብሩን/ታክሱን የመክፈል፣
- ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ግብርን ቀንሶ ማስቀረትና ለመ/ቤቱ ገቢ የማድረግ፣
- በታክስ ደረሰኝና ሌሎች የግብይት ሰነዶች ላይ የገዥውን ወይም የአገልግሎት ተቀባዩን የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የመፃፍ፡፡

## ሙከራ አንድ

- የታክስ ህግ ተገዥነት ማለት ምን ማለት ነው? መገለጫዎችስ ምንድን ናቸው?
- የታክስ ከፋዩን መብት እና ግዴታ አብራሩ?

## 2.2. በታክስ ውሳኔ አለመግባባት ሲፈጠር በየደረጃው አቤቱታ የሚቀርብበት ሂደት

### 2.2.1. የታክስ እና ይግባኝ የሚቀርብባቸው ውሳኔዎች የመጨረሻ ስለመ□ናቸው

- በታክስ ሕግ ሥነ-ሥርዓት መሠረት ካልሆነ በስተቀር:-

- የታክስ ወይም ይግባኝ ሊቀርብበት የሚችል ውሳ□ ወሳኝ እና የመጨረሻ በመሆኑ በማናቸውም ሁኔታ በኮሚሽኑ ወይም በፍርድ ቤት ወይም በሌላ የዳኝነት ሥነ-ሥርዓት ተቃውሞ ሊቀርብበት አይችልም።

## 2.2.2. በታክስ ውሳኔ ላይ ስለሚቀርብ የቅሬታ ማስታወቂያ

- በታክስ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ታክስ ከፋይ የውሳኔውን ማስታወቂያ በደረሰው በ21 ቀናት ውስጥ በውሳኔው ላይ የቅሬታ ማስታወቂያ ለባለሥልጣኑ በጽሑፍ ማቅረብ ይችላል፡፡
- ቅሬታ የቀረበበት የታክስ ውሳኔ በተሻሻለ የታክስ ስሌት ላይ ከሆነ የታክስ ከፋዩ ውሳኔ በተሻሻለ የታክስ ስሌት የመቃወም መብት የመጀመሪያ ውሳኔ የታክስ የመቃወም መብት የመጀመሪያውን የታክስ ስሌት የመቃወም መብት የመጀመሪያውን የታክስ ስሌት በመለወጥ፣ በመቀነስ ወይም በመጨመር በተደረገው ማሻሻያ ላይ ብቻ የተገደበ ይሆናል፡፡

# የቅሬታ ማስታወቂያ...

- ባለሥልጣኑ የቅሬታ ማስታወቂያው በአግባቡ አልቀረበም ብሎ ሲያምን ወይም የቅሬታ ማቅረቢያ ጊዜ ያለፈ እንደሆነ ለታክስ ከፋዩ የጹሑፍ ማስታወቂያ ወዲያውኑ ይሰጠዋል፡፡

- ባለሥልጣኑ፤ ታክስ ከፋዩ በኢትዮጵያ ውስጥ ያልነበረ በመሆኑ በህመም ምክንያት ወይም በሌላ አጥጋቢ ምክንያት በተወሰነው ጊዜ ውስጥ የቅሬታ ማስታወቂያውን ማቅረብ አለመቻሉ እና የቅሬታ ማስታወቂያውን ለማቅረብ በታክስ ከፋዩ በኩል ምክንያታዊ ያልሆነ መዘግየት አለመኖሩ ሲያምንበት የቅሬታ ማቅረቢያ ጊዜው ካበቃበት ቀን ጀምሮ ከ10 ቀናት ላልበለጠ ጊዜ ሊያራዝም ይችላል፡፡

# የቅሬታ ማስታወቂያ…

- የቅሬታ ማመልከቻ ይዘት፤

- የቅሬታውን ፍሬ ነገር ምክንያቶችን፤ የቅሬታ አቅራቢውን ስም፣ የንግድ ፈቃድ፣ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር፣ የምስክር ወረቀት እና አድርሻ፣ ቅሬታ የቀረበበትን የታክስ ውሳኔ ይዘት፣ ውሳኔው የተሰጠበትን ቀን፣ ውሳኔ የሰጠውን ቅ/ጽ/ቤት፣ መያዝ አለበት፤
- ጉዳዩ በታክስ ወኪሉ የሚቀርብ ከሆነ ለወኪሉ ቅሬታ አቅራቢው ውክልና የሰጠበት ማስረጃ ማቅረብ አለበት፤
- ቅሬታውን የሚያስረዳ ሌሎች ኮፒ የሰነድ ማስረጃዎች
- ማመልከቻው እንደቀረበ የሚቆጠረው የቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ የገቢ ማህተም በተደረገበት ቀን ነው።

## የቅሬታ ማስታወቂያ...

- **የቅሬታ ላይ ውሳኔ የሚሰጥበት የጊዜ ገደብ፤**
  - ቅሬታው በቀረበ በ180 ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት፤ ይህ ከተጠናቀቀበት ቀን ጀምሮ ባሉት በ30 ቀናት ውስጥ ለታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ይግባኝ ማቅረብ ይቻላል።
  - በቅሬታው ላይ ለተጨማሪ የማጣራት ሥራ የሚሰጠው ጊዜ ከ1 ወር መብለጥ የለበትም።
- **በቅሬታ ላይ ውሳኔ ስለመስጠት፤**
  - ባለሥልጣኑ የቅሬታውን ውሳኔ ለታክስ ከፋዩ በጹሑፍ የሚያሳውቀው ሲሆን በታክስ ስሌት ላይ የቀረበ ቅሬታ ከሆነ የታክስ ስሌቱን ማሻሻል ጨምሮ ውሳኔውን ለማስፈፀም አስፈለጊ የሆኑትን እርምጃዎች ይወሰዳል።

## 2.2.3. የይግባኝ ኮሚሽን

- **የይግባኝ ማመልከቻ፤**
  - የውሳኔው በደረሰ በ30 ቀናት ውስጥ ማመልከቻ ለኮሚሽኑ ይቀርባል። ኮሚሽኑ የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ሊያራዝም ይችላል።
- **የኮሚሽኑ አሠራር ሥርዓት፤**
  - ፕሬዝዳንቱ በይግባኝ የተነሱትን ጭብጦች ግምት ውስጥ በማስገባት አባላት ይመድባል። ፕሬዚዳንቱ ይግባኙን የክልል የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን እንዲያይ ውክልና ሊሰጥ ይችላል።

**ለኮሚሽኑ ይግባኝ ስለማቅረብ፤**

- ይግባኝ የሚቀርበው በክርክር ላይ ያለ ታክስ ቅጣትና የዘገየ ክፍያ ወለድን ሳይጨምር 50 % የተከፈለ እንደሆነ ብቻ ነው።

# የይግባኝ ኮሚሽን…

- **የኮሚሽኑ ውሳኔ፤**

- ኮሚሽኑ የይግባኝ ማመልከቻ ከቀረበለት ቀን ቀጥለው ባሉት 120 ቀናት ውስጥ በቀረበው ይግባኝ ላይ ውሳኔ ይሰጣል። ፕሬዝዳንቱ ጊዜውን ከ60 ቀናት ላልበለጠ ጊዜ ሊያራዝመው ይችላል። የጊዜ ገደብ ያለመከበር ኮሚሽኑ የሰጠውን ውሳኔ ተቀባይነት አያሳጣውም።

- ኮሚሽኑ የውሳኔውን ግልባጭ ውሳኔው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ባሉት 7 ቀናት ውስጥ ለእያንዳንዱ ተከራካሪ ወገን ይሰጣል።

- ኮሚሽኑ ለታክስ ከፋዩ ከወሰነ፣ ባለሥልጣኑ የተሻሻለ የስሌት ማስታወቂያ መስጠትንም ጨምሮ የውሳኔው ማስታወቂያ በደረሰው 30 ቀናት ውስጥ አስፈላጊ እርምጃዎች ሁሉ መውሰድ ይኖርበታል።

## 2.2.4. ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ስለማቅረብ

- ኮሚሽኑ በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ውሳኔ በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ ይግባኝ ለፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሊያቀርብ ይችላል፡፡ ጊዜውን ፍ/ቤቱ ሊያራዝመው ይችላል፡፡
- በታክስ ስሌት ላይ ከቀረበ ቅሬታ ለፍርድ ቤት ይግባኝ ቀርቧል የሚባለው በክርክር ላይ ያለ ታክስ 75% ሲከፈል ነው፡፡
- ለፍርድ ቤት ይግባኝ የሚቀርበው በሕግ ጉዳዮች ላይ ብቻ ሲሆን የይግባኝ ማስታወቂያውም በቀረበው ይግባኝ የሚነሱት የሕግ ጉዳዮች መግለጽ አለበት፡፡

## 2.2.5. ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ስለሚቀርብ ይግባኝ

- የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ እንደሆነ ውሳኔ በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ የይግባኝ ማስታወቂያውን ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሊያቀርብ ይችላል። ተከራካሪው የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ እንዲራዘምለት በጹሑፍ ማመልከቻ ሲጠይቅ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጊዜውን ሊያራዝመው ይችላል።

**ሙከራ ሁለት**

- በታክስ ውሳኔ አለመግባባት ሲፈጠር በየደረጃው አቤቱታ የሚቀርብበትን ሂደት አብራሩ?

# 2.3. የታክስ ሕጎችን አስቀድሞ መተርጎም

- ሚኒስቴሩ አስገዳጅ የሆኑ በሁሉም ታክስ ከፋዮች ወይም በሁሉም ታክስ ከፋዮች ላይ ተፈጻሚ የሚሆኑ ትርጉሞች ሊሰጥ ይችላል።
- ሚኒስቴሩ በድረ-ገጹ ላይ ማስታወቂያ በማውጣት በሁሉም ታክስ ከፋዮች ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉምን ሊያነሳ ይችላል።
- ሚኒስቴሩ በአንድ ታክስ ከፋይ ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉም ሊሰጥም፣ ላይሰጥም ይችላል። ከሰጠው በድረ-ገጹ ላይ ያወጣል።
- በሚኒስቴሩ የሚሰጥ በአንድ ታክስ ከፋይ ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉም በታክስ ከፋዩ ላይ አስገዳጅ አይሆንም።
- ሚኒስቴሩ በአንድ ታክስ ከፋይ ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉም ለታክስ ከፋዩ የጽሑፍ ማስታወቂያ በመስጠት ሊያነሳ ይችላል።

## 2.4. ለታክስ ወኪሎች ፈቃድ ስለመስጠት

- የታክስ ወኪልነት አገልግሎት ለመስጠት የሚፈልግ ግለሰብ፣ የሽርክና ማህበር/ኩባንያ የታክስ ወኪል ፈቃድ እንዲሰጠው የፀደቀ ቅጽ በመጠቀም ሊያመለክት ይችላል፡፡ አመልካቹ ብቁ እና ተስማሚ ሰው መሆኑን ሲያረጋግጥ ፈቃድ ይሰጠዋል፡፡
- ፈቃድ የተሰጠው ፈቃዱ እንዲታደስለት የአገልግሎት ጊዜ ባበቃ በ21 ቀናት ውስጥ ወይም ባለሥልጣኑ በሚፈቅደው ከዚህ በዘገየ ጊዜ ውስጥ ለባለሥልጣኑ ማመልከት ይችላል፡፡ ፈቃድ ከታደሰበት ቀን ጀምሮ ለ3 ዓመታት ይጸናል፡፡
- ሥራውን ለማቋረጥ የፈለገ ከማቋረጡ በፊት በ7 ቀናት ውስጥ ማሳወቅ አለበት፡፡

## 2.4.1. የታክስ ወኪልነት የፈቃድ ደረጃዎች

- የደረጃ "አንድ" የታክስ ወኪልነት ፈቃድ ለማናቸውም ታክስ ከፋይ አገልግሎት ለሚሰጥ ሰው የሚሰጥ የታክስ ወኪልነት ፈቃድ ነው።

- የደረጃ "ሁለት" የታክስ ወኪልነት ፈቃድ ከደረጃ ሀ ታክስ ከፋዮች በስተቀር ለሌሎች ለማናቸውም ታክስ ከፋዮች አገልግሎት ለሚሰጥ ሰው የሚሰጥ የታክስ ወኪልነት ፈቃድ ነው።

- **ለታክስ ወኪልነት ሙያ ብቁና ተስማሚ ሊያደርጉ የሚችሉ መስፈርቶች፤**

- በታክስ አስተዳደር፣ በአካውንቲንግ፣ በኢኮኖሚክስ፣ በማኔጅመንት፣ በሕግ ወይም በሌላ በተመሳሳይ የትምህርት ዘርፍ ዲግሪ ያለው፣

# ለታክስ ወኪልነት መስፈርቶች…

- የ5 ዓመታት የታክስ ወኪልነት አገልግሎት በመስጠት/እንደ ታክስ ሠራተኛ በማገልገል አግባብነት ያለው የሥራ ልምድ ያለው፤
- የታክስ ወኪል ሥልጠና ኮርስ ፈተና 50 በመቶ እና ከዛ በላይ ውጤት ያመጣና የምስክር ወረቀት ያለው፣ ፈተናውን ያለፈ ለደረጃ አንድ 100 ሺህ ብር፣ ለደረጃ ሁለት 50 ሺህ ብር የመድህን ዋስትና ማቅረብ አለበት፡፡
- የሽርክና ማህበር ሲሆን እያንዳንዱ የማህበሩ አባላት መልካም ጠባይና ሥነምግባር ያለው ስለመሆኑ በባለሥልጣኑ ሲረጋገጥ፤
- ኩባንያ ሲሆን እያንዳንዱ የኩባንያው ዳይሬክተር፣ ሥራ

አስኪያጅና ሌላ ሥራ አስፈፃሚ መልካም ጠባይና ሥነምግባር ያለው ስለመሆኑ በባለሥልጣኑ ሲረጋገጥ፡፡

- ዜግነቱ ኢትዮጵያዊ እና ዕድሜው ከ25 ዓመት በላይ የሆነ፡፡
- ከታክስ ጋር በተያያዘ ማንኛውንም ወንጀል በመፈፀሙ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ያልተረጋገጠ፡፡
- የሙያ ኃላፊነት መድህንን ዋስትና ለማስያዝ አቅም ያለው፤
- በጽሑፍ ቃለ-መሐላ መፈጸም የሚችልና ባለሥልጣኑ በሚወስናቸው የሥልጠና ርዕሶች ቢያንስ ለ240 ሰዓት ሥልጠና መውሰድ ይጠበቅበታል፡፡

## 2.4.2. የታክስ ወኪል የሚመራበት የሥነ ምግባር መርህ

- በታማኝነት ማገልገል፣
- ራስን ከጥቅም ግጭት ማግለል፣
- ጥራት ያለው አገልግሎት መስጠት፣
- ሕግን ማክበር እና ማስከበር፣
- ምስጢር መጠበቅ፣
- ለሙያው ብቁ ሆኖ መገኘት አለበት።

# ክፍል ሶስት፡-

## የታክስ አስተዳደር እና የወንጀል ቅጣቶች

# 3.1. አስተዳደራዊ እና ወንጀል ቅጣቶች ምንነት

## 3.1.1. ቅጣት ማለት፡-

- በማስጠንቀቂያ የተከለከሉ ድርጊቶች በማድረግ (commission) ወይም ማድረግ ግዴታ የሆኑትን ባለማድረግ (omission) ህጉን የተላለፉ ሰዎች ላይ የሚጣል የእርምት ዕርምጃ ነው፡፡
- የታክስ ህግን በመተላለፍ /በመጣስ/ የሚፈጸሙ ጥፋቶች ሁለት ዓይነት ናቸው፡፡
  - አስተዳደራዊ ጥፋት (Administrative fault).
  - የወንጀል ጥፋት (Criminal fault).

# 3.1.2 የወንጀል ጥፋት ማለት

የወንጀል ጥፋት ማለት በህግ የተከለከሉ ድርጊቶች መፈጸም ወይም አድርግ የተባለውን ሆን ብሎ ወስኖ ወይም አስቦ አለመፈጸም ማለት ነው።

የወንጀል ጥፋት ተፈጽሟል ለማለት ሦስት ቅድመ ሁኔታዎች በአንድነት መሟላት አለባቸው እነዚህም፡-

1. ወንጀሉን የሚያቋቁሙት ህጋዊ ፍሬ-ነገሮች (Legal element):
2. ሞራላዊ ፍሬ-ነገሮች (Mental element):
3. ግዙፋዊ ፍሬ ነገሮች (Action or Omission):

የወንጀል ቅጣት ሊለለስከትሉ የሚችሉት ዋናዋና ቅጣቶች፡-

- እስራ ቅጣት
- የግዴታ ቅጣት
- የሞት ቅጣት

# 3.1.3. አስተዳደራዊ ጥፋት

- አንድ ግብር ከፋይ አስተዳደራዊ ጥፋት መፈጸሙን ለማረጋገጥ የህግ ግዴታ ያለበት መሆኑና ግዴታው በህጉ በተመለከተው ጊዜና ሁኔታ (Standard) መሠረት አለመፈጸሙን ብቻ ማረጋገጥ በቂ ሲሆን ግዴታው የተጣለበት ሰው ግዴታውን ያልፈጸመበት ምክንያትና የሀሳብ ሁኔታ በአብዛኛው ከግምት ውስጥ አይገቡም፡፡
- አስተዳደራዊ ቅጣት መቀጣት ከወንጀል ተጠያቂነት ነጻ አያደርግም፤

## 3.2. አስተዳደራዊ ቅጣቶች

- ከምዝገባና ስረዛ ጋር የተያያዙ ቅጣቶች፤

  - መመዝገብ ሲገባው ያልተመዘገበ እንደሆነ መመዝገብ ከነበረበት ጀምሮ እስከተመዘገበበት ቀን ባለው ታክስ 25%፤ የሚከፍለው ታክስ ከሌለ ለእያንዳንዱ ወር/የወሩ ክፊል 1ሺ ብር ይቀጣል።

  - ያለበቂ ምክንያት ምዝገባ እንዲሰረዝለት ያላመለከተ እንደሆነ ምዝገባው እንዲሰረዝለት ማመልከት ከነበረበት ቀን ጀምሮ እስከተሠረዘበት ቀን ድረስ ለእያንዳንዱ ወር ወይም የወሩ ክፊል ለሆነ ጊዜ ብር 1ሺ ቅጣት ይከፍላል።

# አስተዳደራዊ ቅጣቶች...

- **ሰነዶችን ባለመያዝ የሚጣል ቅጣት፤**

- መያዝ የሚጠበቅበትን ሰነድ ያልያዘ፣ ሰነዱ መያዝ በነበረበት የታክስ ዘመን መክፈል ያለበትን ታክስ 20% ቅጣት ይከፍላል።
- መክፈል የሚኖርበት ታክስ የሌለ እንደሆነ ለገቢ ግብር ሲሆን ብር 50ሺ፤ ለሌላ ታክስ ሲሆን ብር 2ሺ የሂሳብ ሰነድ ላልያዘበት ለእያንዳንዱ የታክስ ዘመን ቅጣት ይከፍላል፤
- ከሁለት ዓመት በላይ የሂሳብ ሰነድ ያለመያዝ የንግድ ፈቃድ ስረዛን ያስከትላል፣
- ሰነዶችን ይዞ ማቆየት ላለበት ጊዜ ሳያቆይ የቀረ፤ የደረጃ ‘ሀ’ 50 ሺ ብር፤ የደረጃ ‘ለ’ 20 ሺ ብር ቅጣት ይከፍላል።

## ❑ ከታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር ጋር የተገናኘ ቅጣት፤

- መለያ ቁጥሩን በታክስ ደረሰኝ፣ በታክስ ዴቢት/ክሬዲት ማስታወሻ፣ በታክስ ማስታወቂያ/ በሌላ በማንኛውም ሰነድ ላይ ሳይገልጽ የቀረ መለያ ቁጥር ባልተገለጸበት በእያንዳንዱ ሰነድ 3ሺ ብር ቅጣት ይከፍላል።
- መለያ ቁጥሩን አሳልፎ የሰጠም ሆነ የሌላን የተጠቀመ 10 ብር ይቀጣል። በዚህ ምክንያት ያገኘው የገንዘብ ጥቅም 10ሺ ብር የሚበልጥ ከሆነ የሚከፍለው የገንዘብ ቅጣት መጠን ካገኘው ጥቅም ጋር እኩል ይሆናል።

# አስተዳደራዊ ቅጣቶች...

- **የታክስ ማስታወቂያ ዘግይቶ ማቅረብ ስለሚያስከትለው ቅጣት፤**

- በሕግ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ የታክስ ማስታወቂያ ግዴታውን ያልተወጣ ታክስ ከፋይ ለዘገየበት ለእያንዳንዱ የታክስ ጊዜ ወይም ከፊል ለሆነው ጊዜ ያልተከፈለውን ታክስ 5%፤ 25% እስኪሞላ ድረስ ቅጣት ይከፍላል።

- ለመጀመሪያው የሒሣብ ጊዜ ወይም ከፊል ለሆነው ጊዜ የታክስ ማስታወቂያ ያላቀረበ ሰው የሚከፍለው ቅጣት 50ሺ ብር አይበልጥም።

# አስተዳደራዊ ቅጣቶች…

- ቅጣቱ 10ሺ ብር እና በታክስ ማስታወቂያ ላይ መመልከት ከነበረበት የታክስ መጠን 100% ከዝቅተኛው ያነሰ አይሆንም፡፡
- የሚከፈል ታክስ የሌለ እንደሆነ፣ የታክስ ማስታወቂያ ሳያቀርብ ለዘገየበት ለእያንዳንዱ የታክስ ጊዜ 10ሺ ብር ቅጣት ይከፍላል፡፡

**ታክስን ዘግይቶ መክፈል የሚያስከትለው ቅጣት፤**

- በታክስ መክፈያ ጊዜው ታክስ ሳይከፍል ለቀረ ለዘገየበት ጊዜ፦
- ✓ ለ1 ወር/የወሩ ከፊል ለሆነው ጊዜ ባልተከፈለው ታክስ 5%፤ እና
- ✓ ከዚያ በኋላ ለዘገየበት ለእያንዳንዱ ወር/የወሩ ከፊል ለሆነው ጊዜ ባልተከፈለው ታክስ ላይ ተጨማሪ 2%፤ ቅጣት ይከፈላል፡፡
- ✓ የሚጣለው የቅጣት መጠን ከዋናው የታክስ ዕዳ መብለጥ የለበትም፡፡

# አስተዳደራዊ ቅጣቶች…

- ❑ **ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ተቀንሶ ከሚከፈል ታክስ ጋር በተገናኘ የሚጣል ቅጣት፤**

- ➢ ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ታክስ ቀንሶ ለባለሥልጣኑ ማስተላለፍ ያለበት ሰው ሳይቀንስ የቀረው ወይም ቀንሶ ለባለሥልጣኑ ያላስተላለፈውን ታክስ 10% ቅጣት ይከፍላል። ለድርጅት ተፈጻሚ በሚሆንበት ጊዜ፣ ከሚጣለው ቅጣት በተጨማሪ የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ፣ ዋና የሂሳብ ሹም ወይም ታክስ ተቀንሶ መያዝ እንዳለበትና የተያዘውም ታክስ መከፈል እንዳለበት የማረጋገጥ ኃላፊነት ያለበት ሌላ የድርጅቱ ሠራተኛ እያንዳንዳቸው 2ሺ ብር ቅጣት ይከፍላሉ።

# አስተዳደራዊ ቅጣቶች...

- ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ተቀንሶ የሚከፈልን ታክስ ለማስቀረት በማሰብ ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ታክስ ቀንሶ የመክፈል ግዴታ ላለበት ሰው ዕቃዎችን/አገልግሎቶችን ለማቅረብ ፈቃደኛ ካልሆነ 10ሺ ብር ይቀጣል።

- ግብር ቀንሶ ገቢ ያላደረገ የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ፣ ዋና የሒሳብ ሹም ወይም ዋና ሒሳብ ሹም የሌለ እንደሆነ ታክስ ቀንሶ መያዝ እንዳለበትና የተያዘውም ታክስ መክፈል እንዳለበት የማረጋገጥ ኃላፊነት ያለበት ሌላ የድርጅቱ ሠራተኛ በእያንዳንዱ የታክስ መክፈያ ጊዜ ተቀንሶ ገቢ ላልተደረገ ግብር እያንዳንዳቸው 2ሺ ብር ቅጣት ይከፍላሉ።

## አስተዳደራዊ ቅጣቶች…

- ከተጨማሪ እሴት ታክስ ጋር የተያያዙ ቅጣቶች፤

|.ለተ.እ.ታ. መመዝገብ ያለበት ሰው ሳይመዘገብ የቀረ እንደሆነ፣ መመዝገብ ከነበረበት ቀን ጀምሮ ለመመዝገብ እስካመለከተበት ቀን/በባለሥልጣኑ አነሳሽነት እስከተመዘገበበት ድረስ ላለው ለእያንዳንዱ ወር/የወሩ ከፊል ለሆነው ጊዜ 2ሺ. ብር ይቀጣል።

||. በዚህ ተራ ቁጥር (|) መሠረት መመዝገብ ከነበረበት ቀን ጀምሮ ለመመዝገብ እስካመለከተበት ቀን ወይም በባለሥልጣኑ አነሳሽነት እስከተመዘገበበት ቀን ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ በፈጸመው የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ላይ ሊከፈል ይገባ የነበረውን የተጨማሪ እሴት ታክስ 100% (መቶ በመቶ) ቅጣት ይከፍላል።

# አስተዳደራዊ ቅጣቶች…

III.በተራ ቁጥር (II) መሠረት የሚጣል ቅጣት በተራ ቁጥሩ በተገለጸው ጊዜ ውስጥ ታክስ ከፋዩ በፈጸመው የተ.እ.ታ. የሚከፈልበት ግብይት ላይ ሊከፈል ይገባ የነበረውን የተ.እ.ታ. አያስቀርም። ሆኖም ታክስ ከፋዩ በዚህ ጊዜ ውስጥ ባከናወነው ግብይት ላይ የከፈለው የተርን ኦቨር ታክስ ካለ ሊከፍል ከሚገባው የተ.እ.ታ. ላይ ተቀናሽ ይደረግለታል።

IV.ሆን ብሎ በግብይቱ ላይ መከፈል የሚገባውን የተ.እ.ታ. ለማሳነስ ወይም በግብይቱ ላይ ተመላሽ የሚደረገውን የታክስ መጠን ለመጨመር በማሰብ ትክክለኛ ያልሆነ የታክስ ደረሰኝ የሰጠ እንደሆነ 50ሺ ብር ቅጣት ይከፍላል።

# አስተዳደራዊ ቅጣቶች...

- **የታክስ ደረሰኝ አለመስጠት**

- ደረሰኝ መስጠት ሲገባው ያልሰጠ ማንኛውም ታክስ ከፋይ ለገዥ ባልሰጠው በእያንዳንዱ ደረሰኝ ብር 50ሺ ቅጣት ይቀጣል።

- **ታክስን አሳንሶ ማሳወቅ የሚያስከትለው ቅጣት**

- በታክስ ማስታወቂያ የተገለጸው የታክስ መጠን ታክስ ከፋዩ ሊከፍል ከሚገባው ትክክለኛ የታክስ መጠን ያነሰ እንደሆነ የታክስ ጉድለቱን መጠን 10% ይቀጣል። ለ2ኛ ጊዜ ሲሆን የቅጣቱ መጠን ወደ 30 ከፍ ይላል፤ ለ3ኛ ጊዜ እና ከዚያ በላይ ተፈጻሚ በሚሆንበት ጊዜ የቅጣቱ መጠን ወደ 40% ከፍ ይላል።

# አስተዳደራዊ ቅጣቶች...

- **ታክስን በመሸሸ የሚጣል ቅጣት፤**

  - ባለሥልጣኑ የታክስ ከፋይን የታክስ ስሌት ሲሠራ ከታክስ መሸሸን የሚከላከል ድንጋጌ ተፈጻሚ ካደረገ ታክስ ከፋዩ ይህ ድንጋጌ ተፈጻሚ ባይደረግ ኖሮ ከታክስ በመሸሸ ሊያስቀር ይችል የነበረውን የታክስ መጠን እጥፍ ቅጣት ይከፍላል።

- **የኤሌክትሮኒክስ የታክስ ሥርዓትን ባለመከተል የሚጣል ቅጣት**

  - የታክስ ማስታወቂያውን/ክፍያውን በኤሌክትሮኒክስ የታክስ ሥርዓት መሠረት እንዲፈጽም ማስታወቂያ የደረሰው፤ ከደረሰው ቀን ጀምሮ ባሉት 14 ቀናት ውስጥ ባለሥልጣኑን የሚያሳምን በቂ ምክንያት ማቅረብ ካልቻለ 50ሺ ብር ይቀጣል።

# አስተዳደራዊ ቅጣቶች...

- **በታክስ ወኪል ላይ ስለሚጣል ቅጣት፤**

➢ የታክስ ወኪልነት ፈቃድ የተሰጠው ሰው፦

✓ ለደንበኛው የምስክር ወረቀት/መግለጫ ካልሰጠ፤ ወይም ለደንበኞች የተሰጡ የምስክር ወረቀቶችንና መግለጫዎችን ለተወሰነው ጊዜ ካልያዘ፤ ወይም የታክስ ወኪልነት ሥራውን ማቆሙን ለባለሥልጣኑ ካላሳወቀ፤ ብር 10ሺ ቅጣት ይከፍላል።

- **መረጃ ያለመስጠት የሚያስከትለው ቅጣት፤**

መረጃ የመስጠት ግዴታ ያለበት ባለሥልጣኑ በጽሑፍ ሲጠይቀው የተጠየቀውን መረጃ ያላቀረበ እንደሆነ መረጃውን ያልሰጠው ሰው ወይም መረጃ የተጠየቀው መ/ቤት የበላይ ኃላፊ 5ሺ ብር ይቀጣል።

# አስተዳደራዊ ቅጣቶች...

- **ከሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ጋር ተያይዞ የሚጣል ቅጣት፤**

➢ በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ የመጠቀም ግዴታ ያለበት ሰው፦

✓ ዕውቅና ያልተሰጠው ወይም በባለሥልጣኑ ዘንድ ያልተመዘገበ መሣሪያ ወይም የሽያጭ ነቁጣ ሶፍትዌር ሲጠቀም ከተደረሰበት ለተጠቀመበት ለእያንዳንዱ መሣሪያ 50ሺ ብር ቅጣት ይከፍላል፤

✓ መሣሪያው በጥገና ላይ ባለበት ጊዜ/በሌላ በቂ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር በሽ.መ.መ. ከታተመ ደረሰኝ ውጪ በሌላ ማናቸውም ዓይነት ደረሰኝ ግብይት ካከናወነ ብር 50ሺ ብር ቅጣት ይከፍላል፤

# አስተዳደራዊ ቅጣቶች...

- የሽ.መ.መ. የጉዳት/የፊስካል ማስታወሻ እንዲቀየር ያደረገ/ጉዳት ለማድረስ/ማስታወሻውን ለመቀየር የሞከረ 100ሺ. ብር ይቀጣል።
- የሽ.መ.መ. ሥርዓት ኦዲት እንዳይደረግ መሰናክል የፈጠረ/ በዓመት 1 ጊዜ በአገልግሎት ማዕከል የቴክኒክ ምርመራ ያላደረገ 25ሺ. ብር ይቀጣል።
- የሽ.መ.መ. ከአገልግሎት ማዕከል ጋር ውል ካልፈጸመ/ከተርሚናል ጋር ሳያያይዝ ከተጠቀመ/የምርመራ መዝገብ ከመሣሪያው ጎን የላስቀመጠ/የተመዘገቡ ዕቃዎች ተመላሽ መደረጋቸው/ደንበኛው የተመላሽ ጥያቄ ማቅረቡ በተመላሽ መዝገብ በትክክል መመዝገቡ ሳይረጋገጥ የተመላሽ ደረሰኝ ከሰጠ 25ሺ. ብር ይቀጣል።

# አስተዳደራዊ ቅጣቶች…

- መሣሪያው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት አገልግሎት መስጠት ሲያቋርጥ በ3 ቀናት ጊዜ ውስጥ ወይም በሌላ ማናቸውም ምክንያት ብልሽት ባጋጠመው በ4 ሰዓት ውስጥ ለአገልግሎት ማዕከሉ እና ለባለሥልጣኑ ካላሳወቀ 10ሺ. ብር ይቀጣል፤
- የሽ.መ.መ. የሚቀመጥበትን ትክክለኛ አድራሻ ለባለሥልጣኑ ያላስታወቀ 50ሺ. ሺ. ብር ይቀጣል፤
- የአድራሻ/የስም ለውጥ ሲያደርግ/የንግድ ሥራውን የሚያቋርጥ ሲሆን ከ3 ቀናት አስቀድሞ ለአገልግሎት ማዕከሉ እና ለባለሥልጣኑ ያላሳወቀ 25ሺ. ሺ. ብር ቅጣት ይከፍላል።

# አስተዳደራዊ ቅጣቶች...

- መሣሪያው ጥቅም ላይ በሚውልበት የንግድ ሥራ ቦታው፦
  - ✓ የተጠቃሚውን ስም፣ የንግድ ስም፣ ንግዱ የሚካሄድበትን አድራሻ፣ መለያ ቁጥሩን፣ መሣሪያውን የዕውቅና እና መጠቀሚያ ፈቃድ ቁጥር፤
  - ✓ "የሽያጭ ሠራተኞች መሣሪያው የተበላሸ ከሆነ በባለሥልጣኑ ፈቃድ የታተመ ተከታታይ ቁጥር ያለው ደረሰኝ ለደንበኞች የመስጠት ግዴታ አለባቸው"ና "ደረሰኝ የማይሰጥ ከሆነ አይክፈሉ" የሚል ጽሑፍ፤ በሚታይ ቦታ ካልተለጠፈ 10ሺ ብር ይቀጣል።
- ሥራ ላይ የዋለውን የሽያጭ ነቁጣ ሶፍትዌር የባለሥልጣኑ ዕውቅና ባልተሰጠው ሰው ያስቀየረ/ያሻሻለ 30ሺ ብር ይቀጣል።

# አስተዳደራዊ ቅጣቶች...

❑ **ልዩ ልዩ ቅጣቶች**

- ማንኛውንም ለውጥ ያላሳወቀ 20ሺ ሺ ብር ቅጣት ይከፍላል፡፡
- የመመስረቻ ጽሑፉን፣ መተዳደሪያ ደንቡን፣ የሽርክና ስምምነቱን፣ ወይም ሌላ የመመስረቻ ወይም የምዝገባ ሰነድ ወይም በእነዚህ ሰነዶች ላይ የተደረገውን ማንኛውም ማሻሻያ ሳያቀርብ የቀረ ድርጅት ሰነዱ ሳይቀርብ ለቀረበት ለእያንዳንዱ ወር ወይም የወሩ ከፊል ለሆነው ጊዜ 10ሺ ብር ቅጣት ይከፍላል፡፡
- የኦዲት ሪፖርቱን ለባለሥልጣኑ ያላቀረበ ማንኛውም ኦዲተር ሰነዱ ሳይቀርብ ለቀረበት ለእያንዳንዱ ወር ወይም የወሩ ከፊል ለሆነው ጊዜ ብር 10ሺ ብር ቅጣት ይከፍላል፡፡

# አስተዳደራዊ ቅጣቶች...

- በኢትዮጵያ ነዋሪ ካልሆነ ሰው ጋር የተደረገን ውል ያላሳወቀ፤ ሳያሳውቅ ለቀረበት ለእያንዳንዱ ቀን 1ሺ ብር ይቀጣል።
- ግንኙነት ካለው ሰዎች ጋር የሚያደርጋቸውን ግብይቶች ዝርዝር ጉዳይ ለባለሥልጣኑ ያልገለጸ ሰው ብር 100ሺ ብር ይቀጣል።
- ማናቸውም መረጃ የመስጠት ግዴታ ያለበት ሰው ባለስልጣኑ የሚጠይቀውን መረጃ ለባለሥልጣኑ ያልሰጠ እንደሆነ እንደሁኔታው መረጃውን ያልሰጠው ሰው ወይም መረጃ የተጠየቀው መስሪያቤት የበላይ ኃላፊ 5ሺ ብር ቅጣት ይከፍላል።

# 3.3. የታክስ ወንጀል ጉዳዮች የሚታዩበት ሥነ-ሥርዓት

❑ **ከታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር ጋር የተገናኙ ወንጀሎች**

➢ ከ1 በላይ መለያ ቁጥር የወሰደ/ለመውሰድ የሞከረ፤ የመለያ ቁጥሩን ሌላ ሰው እንዲጠቀምበት የሰጠ፤ የሌላን ሰው መለያ ቁጥር የተጠቀመ፤ 20ሺ ብር እና ከ1-3 ዓመት ቀላል እሥራት ይቀጣል፡፡

❑ **የሀሰት ወይም አሳሳች መግለጫዎች እና የተጭበረበሩ ሰነዶች**

ለባለሥልጣኑ፤ ሆነ ብሎ/በከባድ ቸልተኝነት፤ ሀሰተኛ/አሳሳች መግለጫ የሰጠ፤/ሊቀርብ የሚገባን መግለጫ መካተት የሚገባቸውን ነገሮች ያለበቂ ምክንያት ያስቀረ፤ የተጭበረበሩ ሰነዶችን ያቀረበ፤ ከ50ሺ-100ሺ ብር እና ከ3 ዓመት-15 ዓመት ጽኑ እሥራት ይቀጣል፡፡

## ወንጀል…

- **የተጭበረበሩ ወይም ሕገ-ወጥ የሆኑ ደረሰኞች**

I.የተጭበረበሩ ደረሰኞችን ያዘጋጀ፣ ያተመ፣ የሸጠ/ያሰራጨ፤ የታክስ ዕዳውን ለመቀነስ/ተመላሽ ለመጠየቅ የተጭበረበሩ ደረሰኞችን የተጠቀመ፤ 100ሺ ብር እና ከ7-10 ዓመት ጽኑ እሥራት ይቀጣል።

II.በተራ ቁጥር (I) የተጠቀሱትን የተጭበረበሩ ደረሰኞች በመጠቀም የተገኘው የገንዘብ ጥቅም ከ100ሺ ብር የሚበልጥ፣ በዚህ ተራ ቁጥር (I) መሠረት የሚጣለው ቅጣት ከገንዘቡ ጥቅም ጋር እኩል በሆነ የገንዘብ ቅጣት እና ከአስር ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይሆናል።

## ወንጀል...

|||.ሀሰተኛ ደረሰኞችን ለመሥራት፣ ለማዘጋጀት/ለማተም የሚያገለግል ማሽን፣ መሣሪያ፣ ሶፍትዌር የያዘ፣ የሸጠ፣ ያከራየ፣ /በሌላ መንገድ ያቀረበ ማንኛውም ሰው 200ሺ ብር ቅጣት እና ከ10- 15 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል፡፡

|V.በተራ ቁጥር (|||) መሠረት ጥፋተኛ ሆኖ መገኘት ማሽኑን፣ መሣሪያውን፣ ሶፍትዌሩን/የወንጀሉን ፍሬ መውረስን ያስከትላል፡፡

V.ሀሰተኛ ደረሰኞችን የያዘ፣ ያስቀመጠ፣ ለሽያጭ ያመቻቸ፣/ሀሰተኛ ደረሰኞች ጥቅም ላይ እንዲውሉ ያደረገ ሰው ከ3 እስከ 3 ዓመት በሚደረስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል፡፡

## ወንጀል…

- ከደረሰኝ ጋር የተገናኙ ጠቅላላ ወንጀሎች፤

I.ማንኛውም ደረሰኝ የመስጠት ግዴታ ያለበት ያለደረሰኝ ግብይት ያከናወነ እንደሆነ ከ25ሺ-50ሺ ብር እና ከ3-5 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል።

II.በአንድ ግብይት በተሰጡ ተመሳሳይ የደረሰኝ ኮፒዎች ላይ የተለያዩ ዋጋዎችን በመመዝገብ የሽያጭ ዋጋን ያሳነሰ ማንኛውም ሰው 100ሺ ብር እና ከ5-7 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል።

III.የሽያጩ ትክክለኛ ዋጋ ከ100ሺ ብር የሚበልጥ ከሆነ በተራ ቁጥር (II) መሠረት የሚጣለው ቅጣት በደረሰኞቹ ላይ ከተመለከቱት ከፍተኛው የገንዘብ መጠንና ከ7-10 ዓመት ጽኑ እሥራት ይቀጣል።

## ወንጀል...

|V. ግብይት ሳይፈጸም ደረሰኝ የሰጠ/የተቀበለ ሰው ከ100ሺ-200ሺ ብር እና ከ7-10 ዓመት ጽኑ እሥራት ይቀጣል፡፡ ደረሰኙ ከ200ሺ ብር የሚበልጥ የገንዘብ መጠን ከያዘ በተራ ቁጥር (|) መሠረት የሚጣለው ቅጣት በደረሰኙ ከተገለጸው የገንዘብ መጠን ጋር እኩል በሆነ የገንዘብ ቅጣት እና ከ10-15 ዓመት ጽኑ እሥራት ይቀጣል፡፡

V. ባለሥልጣኑ ሳይፈቅድለት የታክስ ደረሰኝ ያተመ ሰው ከ300ሺ-500ሺ ብር በሚደርስ የገንዘብ ቅጣት እና ከ2-5 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል፡፡ በዚህ መሠረት ጥፋተኛ የተባለ ወንጀሉን ለ2ኛ ጊዜ ፈጽሞ ጥፋተኛ መሆኑ ከተረጋገጠ የህትመት መሣሪያው እና የማተሚያ ድርጅቱ ይወረሳል፣ የንግድ ፈቃዱም ይሰረዛል፡፡

## ወንጀል...

- **ሕገ-ወጥ የሆነ ተመላሽን/ከተገቢው በላይ ማካካሻን መጠየቅ፤**

➢ ባለሥልጣኑን ለማጭበርበር በማሰብ ተመላሽ/ማካካሻ የጠየቀ ሰው 50ሺ ብር እና ከ5-7 ዓመት ጽኑ እሥራት ይቀጣል።

- **ከተጨማሪ እሴት ታክስ ጋር የተያያዙ ወንጀሎች፤**

➢ ለተ.እ.ታ. ሳይመዘገብ የታክስ ደረሰኝ የሰጠ ሰው 200ሺ ብር እና ከ7-10 ዓመት ጽኑ እሥራት ይቀጣል።

➢ የታክስ ዴቢት/ክሬዲት ማስታወሻ ለመስጠት ፈቃደኛ ካልሆነ፤/ከተፈቀደው ውጪ የታክስ ዴቢት/ክሬዲት ማስታወሻ የሰጠ፤ 10ሺ ብር እና በ1 ዓመት ቀላል እሥራት ይቀጣል።

# ወንጀል…

- ❑ **ከቴምብር ቀረጥ ጋር የተያያዙ ወንጀሎች**

- ➢ በምስክርነት ካልሆነ በስተቀር የቴምብር ቀረጥ ሊከፈልበት ሲገባ የቴምብር ቀረጥ ያልተከፈለበትን ሰነድ ሥራ ላይ ያዋለ/የፈረመ፤ ወይም የቴምብር ቀረጥ ላለመክፈል/አነስተኛ የቴምብር ቀረጥ ለመክፈል በማሰብ የአንድን ሰነድ ትክክለኛ ባህሪ ያልገለጸ/የደበቀ፤ ከ25ሺ-50ሺ ብርና ከ3-5 ዓመት ጽኑ እሥራት ይቀጣል፡፡

- ➢ ቴምብሮችን/ቴምብር የተመታባቸውን ሰነዶች ለመሸጥ የተፈቀደለት ሆኖ የቴምብር ቀረጥ አዋጁን ወይም ደንቡን የተላለፈ፤/ቴምብሮችን ወይም ቴምብር የተመታባቸውን ሰነዶች ሳይፈቀድለት የሸጠ/ ለሽያጭ ያቀረበ፤ ከ5ሺ-25ሺ ብር እና ከ3-5 ዓመታት ጽኑ እሥራት ይቀጣል፡፡

## ወንጀል...

- **ታክስን ለማስከፈል ከሚወሰድ እርምጃ ጋር የተያያዙ**

|.ማንኛውም የታክስ ከፋይ ንብረት ተረካቢ ግዴታውን ሳይፈፅም ከቀረ፤ በ5ሺ ሺ ብር እና በ1 ዓመት ቀላል እሥራት ይቀጣል፡፡

||.ትዕዛዙ የተላለፈበትን ንብረት የሸጠ፣ የለወጠ፣/በሌላ መንገድ ያስተላለፈ፤ ትዕዛዙ የተላለፈበትን ንብረት የደበቀ፣ የሰበረ፣ ያበላሸ/የጎዳ፤/ትዕዛዙ የተላለፈበትን ንብረት የሚመለከት ሰነድ ያወደመ፣ የደበቀ፣ ያስወገደ፣ የጎዳ፣ የለወጠ፣ የሰረዘ፣ የደለዘ/ያጠፋ፤ ከ2-3 ዓመት ቀላል እሥራት ይቀጣል፡፡

|||. ለ3ኛ ወገን በሚሰጥ ክፍያ ትዕዛዝ መሠረት የተጠየቀውን ገንዘብ ለባለሥልጣኑ ያልከፈለ ከ2- 3 ዓመት ቀላል እሥራት ይቀጣል፡፡

## ወንጀል...

V.ለ3ኛ ወገን የሚሰጥ የገንዘብ ክፍያ ትዕዛዝ የደረሰው ሰው፤ ትዕዛዙን መፈጸም እንደማይችል ለባለሥልጣኑ ካሳወቀ፣ ባለሥልጣኑ የሰጠውን ትዕዛዝ መሻሩን/ማሻሻሉን/ትዕዛዙ የደረሰው ሰው ያቀረበውን ማስታወቂያ ውድቅ ማድረጉን እስካላስታወቀው ድረስ ለ3ኛ ወገን የሚሰጥ የገንዘብ ክፍያ ትዕዛዝ የተሰጠው ሰው ትዕዛዙን እንደፈጸመ ይቆጠራል።

V.ከሃገር የመውጣት ክልከላ ትዕዛዝን በመጣስ ከኢትዮጵያ የወጣ ወይም ለመውጣት የሞከረ ማንኛውም ሰው ከ2-3 ዓመት ቀላል እሥራት ይቀጣል።

# ወንጀል...

VI. የተላለፈን ትዕዛዝ ያላከበረ ማንኛውም የፋይናንስ ተቋም በዚህ ምክንያት ባለሥልጣኑ ሳይሰበስበው በቀረው የገንዘብ ልክ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

VII. የተላለፈን ትዕዛዝ ያላከበረ ማንኛውም የፋይናንስ ተቋም በዚህ ምክንያት ባለሥልጣኑ ሳይሰበስበው በቀረው የገንዘብ ልክ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡ ይህ ወንጀል የተፈጸመው የፋይናንስ ተቋሙ ሥራ አስኪያጅ እያወቀ/በቸልተኝነቱ ምክንያት ከሆነ ሥራ አስኪያጁ ከ2-3 ዓመት በሚደርስ ቀላል እሥራት ይቀጣል፡፡

IX. ፈቃድ ሳይገኝ፤ የእሽግ ትዕዛዝ የተላለፈበትን የንግድ ሥፍራ/ቦታ እሽግ የከፈተ/ያስወገደ ከ2-3 ዓመት ቀላል እሥራት ይቀጣል፡፡

## ወንጀል...

- **ታክስን ስለመሰወር**

  - ታክስን ለመሰወር በማሰብ ገቢውን የደበቀ፣ የታክስ ማስታወቂያውን ያላቀረበ/ታክሱን ያልከፈለ ከ100ሺ-200ሺ ብር እና ከ3-5 ዓመት ጽኑ እሥራት ይቀጣል።

  - ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ታክስን ቀንሶ ገቢ የማድረግ ኃላፊነት የተጣለበት ታክስን ለመሰወር በማሰብ ቀንሶ የያዘውን ታክስ ለባለሥልጣኑ ካላስተላለፈ ከ3-5 ዓመት ጽኑ እሥራት ይቀጣል።

- **የታክስ ሕጎችን አስተዳደር ስለማደናቀፍ**

  - ግዴታውን እየተወጣ ያለን የታክስ ሠራተኛ ያደናቀፈ/ለማደናቀፍ የሞከረ ከ1-3 ዓመት ቀላል እሥራት ይቀጣል።

## ወንጀል...

- የታክስ ሕግ አስተዳደርን ያደናቀፈ/ለማደናቀፍ የሞከረ ከ10ሺ ብር በማያንስ ገንዘብ እና ከ3-5 ዓመት ጽኑ እሥራት ይቀጣል።

**❑ ሥልጣን ሳይኖር ታክስ መሰብሰብ**

- ታክስ እንዲሰበስብ ሥልጣን ያልተሰጠው፤ ማንኛውንም ታክስ የሰበሰበ/ለመሰብሰብ ከሞከረ ከ50ሺ-75ሺ ብር እና ከ5-7 ዓመት ጽኑ እሥራት ይቀጣል።

**❑ በታክስ ወንጀል መርዳት ወይም ማበረታታት**

በታክስ ሕግ "ዋና ወንጀል" አድራጊ ተብሎ የሚታወቅ ሌላ ሰው እንዲፈጽም የረዳ፣ ያበረታታ፣ ያገዘ፣ ያነሳሳ ወይም የተመሳጠረ እንደሆነ በዋናው ወንጀል አድራጊ ላይ የተጣለውን ቅጣት ይቀጣል።

## ወንጀል…

- ከታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ጋር የተያያዙ ወንጀሎች

- በታክስ ይግባኝ ኮሚሽን አባልነቱ ኃላፊነቱን በመፈጸም ላይ ያለን ሰው የሰደበ፤ ፈቃድ ሳይኖረው የኮሚሽኑን የሥራ ሂደት ያቋረጠ፤ የኮሚሽኑን የሥራ ሂደት ለማወክ በማሰብ በኮሚሽኑ ግቢ ውስጥ ወይም ኮሚሽኑ ባለበት አካባቢ ረብሻ የፈጠረ ወይም በረብሻው የተሳተፈ፤ ወይም በማናቸውም ሁኔታ የኮሚሽኑን ሥራ ያሰናከለ እንደሆነ፤ ከ500-3ሺ ብር ወይም ከ6 ወር-2 ዓመት ቀላል እሥራት ይቀጣል።

- ለኮሚሽኑ እያወቀ ሀሰተኛ/አሳሳች ማስረጃ የሰጠ ከ50ሺ ብር በማያንስ እና ከ3-5 ዓመት ጽኑ እሥራት ይቀጣል።

## ወንጀል…

- በኮሚሽኑ ፊት እንዲቀርብ/ለኮሚሽኑ ሰነድ እንዲያቀርብ/መረጃ እንዲሰጥ መጥሪያ ሲደርሰው ያለበቂ ምክንያት በመጥሪያው መሠረት ያልፈጸመ፤ በኮሚሽኑ ፊት ያለምንም በቂ ምክንያት ቃለ-መሃላ ለመፈጸም/እውነትን ለመመስከር ማረጋገጫ ለመስጠት ፈቃደኛ ያልሆነ፤ ኮሚሽኑ በሚያየው ጉዳይ ለቀረበለት ጥያቄ ያለ በቂ ምክንያት መልስ ለመስጠት ፈቃደኛ ያልሆነ፤ ከ300 ብር-3ሺ ብርና ከ6 ወር-2 ዓመት ቀላል እሥራት ይቀጣል።

### ❑ በታክስ ወኪሎች ስለሚፈፀም ወንጀል

- ያለፈቃድ የታክስ ወኪልነት አገልግሎት የሰጠ እንደሆነ ከአንድ ዓመት እስከ ሦስት ዓመት በሚደርስ ቀላል እሥራት ይቀጣል።

## ወንጀል…

- ❑ **ከሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪዎች ጋር በተገናኘ የሚፈጸሙ ወንጀሎች፤**

- ➢ ዕውቅና ያልተሰጠው/ያልተመዘገበ የሽ.መ.መ. ከተጠቀመ ከ3-7 ዓመት ጽኑ እሥራት ይቀጣል፤

- ➢ መሣሪያው በጥገና ላይ ባለበት ጊዜ/በሌላ በቂ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር በሽ.መ.መ. ከታተመ ደረሰኝ ውጪ/ያለደረሰኝ ግብይት ካከናወነ፣ ከ2-5 ዓመት ጽኑ እሥራት ይቀጣል፤

- ➢ በመሣሪያው የፊስካል ማስታወሻ ላይ ጉዳት ያደረሰ/የፊስካል ማስታወሻ እንዲቀየር ያደረገ/ጉዳት ለማድረስ/ማስታወሻውን ለመቀየር ሙከራ ካደረገ፣ ከ3-5 ዓመት ጽኑ እሥራት ይቀጣል።

# ወንጀል...

- የሽ.መ.መ./ሶፍትዌር አቅራቢነት ፈቃድ ሳይኖረው የሽ.መ.መ. /ሶፍትዌር ለገበያ ያዋለ ከ5-7 ዓመት ጽኑ እሥራት ይቀጣል።

- የሽ.መ.መ. የአገልግሎት ማዕከል አቅራቢው ዕውቅና ያልሰጠውን እና በባለሥልጣኑ ያልተመዘገበ ሠራተኛ ያሠራ በ50ሺ. ብር የገንዘብ ቅጣት/ከ1 ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት ይቀጣል።

- የሽ.መ.መ. የፈታ/የገጣጠመ/የማዕከል ሠራተኛ በሌለበት ሥራ ላይ እንዲውል የፈቀደ/የመሣሪያውን መለያ ቁጥር የቀያየረ፤/ በተጠቃሚው/በማዕከሉ/በሠራተኛው/በአቅራቢው የተፈጸመን ሕገ-ወጥ ድርጊት በ24 ሰዓት ውስጥ ለባለሥልጣኑ ሪፓርት ያላደረገ፤ ከ5ሺ. ብር በማይበልጥና ከ1-3 ዓመት ጽኑ እሥራት ይቀጣል።

## 3.4. ሽልማቶች

ማንኛውም ሰው በመደበቅ፣ አሳንሶ በማሳወቅ፣ በማጭበርበር/በሌላ ተገቢ ባልሆነ መንገድ የሚፈፀምን የታክስ ስወራ አስመልክቶ ሊረጋገጥ የሚችል ተጨባጭና የማያሻማ መረጃ ለባለሥልጣኑ የሰጠ እንደሆነ፤ የተሰወረውን ታክስ መጠን እስከ 20% በሽልማት መልክ ታክሱ በሚሰበሰብበት ጊዜ ለዚህ ሰው ይሰጣል፡፡ ይህ በታክስ ስወራው ተግባር ላይ ለተሳተፈ፣ ወይም የታክስ ስወራውን ማሳወቅ የመደበኛ ሥራው አካል ለሆነ ሰው ተፈፃሚ አይሆንም፡፡

### ሙከራ ሶስት

- ❑ በታክስ የሚፈጸሙ የአስተዳደራዊ እና የወንጀል ቅጣቶች እንዲሁም ሽልማቶች አብራሩ?

# ክፍል አራት፡- አስተዳደራዊ ቅጣት አነሳስ

## 4.1. ዝቅተኛ፣ መካከለኛ እና ከፍተኛ የቅጣት ደረጃ አነሳስ

- **ዝቅተኛ የቅጣት ደረጃ (ከ30-90%) ይነሳል**
  - ከምዝገባ እና ስረዛ ጋር የተያያዙ ቅጣቶች፤
  - ከታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር ጋር የተገናኘ ቅጣት፤
  - ታክስን ዘግይቶ ማሳወቅ እና ዘግይቶ መክፈል።

- **መካከለኛ የቅጣት ደረጃ (ከ20-80%) ይነሳል**
  - ከተከፋይ ሒሣብ ላይ ተቀንሶ ከሚከፈል ታክስ ጋር በተገናኘ የሚጣል ቅጣት፤
  - ከሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ጋር ተያይዞ የሚጣል ቅጣት፤

# ዝቅተኛ፣ መካከለኛ እና ከፍተኛ የቅጣት ደረጃ አነሳስ...

- የባንክና የማሽን አድራሻ ለውጥ ያላሳወቀ ታክስ ከፋይ ብር 20ሺ እና ግንኙነት ካለው ሰዎች ጋር የሚያደርጋቸውን ግብይቶች ዝርዝር ጉዳይ ለባለሥልጣኑ ያልገለጸ ሰው ብር 10ሺ ሲቀጣ።

- **ከፍተኛ የቅጣት ደረጃ (ከ10-70%) ይነሳል**

- ሰነዶችን ባለመያዝ የሚጣል ቅጣት፣ የታክስ ደረሰኝ ባለመስጠት ብር 50ሺ ሲቀጣ እና ታክስን በመሸሸ ሲቀጣ፤

- ለታክስ ሰብሳቢው የተጠየቀ መረጃ ባለመስጠት 5ሺ ሲቀጣ።

- ሆን ብሎ በግብይቱ ላይ መከፈል የሚገባውን VAT ለማሳነስ/ በግብይቱ ላይ ተመላሽ የሚደረገውን የታክስ መጠን ለመጨመር በማሰብ ትክክለኛ ያልሆነ የታክስ ደረሰኝ የሰጠ ብር 50ሺ ሲቀጣ፤

## 4.2. የአስተዳደራዊ ቅጣት በከፊል የሚነሳበት መስፈርት እና መጣኔ

| ተ.ቁ | ፍሬ፣ወለድና መቀጮ የተከፈለበት ግዜ | የቅጣት አነሳስ ምጣኔ በደረጃ መሰረት | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ዝቅተኛ | መካከለኛ | ከፍተኛ |
| 1 | **ታክስ ከፋዩ፤- ማስታወቅያ፣የቅሬ፣የፍ/ቤት ውሳኔ ደርሶት** | | | |
| | **በ30 ቀናት ውስጥ ቀርቦ ከከፈለ** | 90 | 80 | 70 |
| | **ውል ገብቶ በ6 ወራት ውስጥ ከፍሎ ካጠናቀቀ** | 80 | 70 | 60 |
| | ውል ገብቶ ከ6 ወራት በላይ ከፈጀበት | 70 | 60 | 50 |
| 2 | **ባለመክፈሉ ማስጠንቀቂያ ሳይደርሰው ንብረቱ ከተያዘ በኋላ** | | | |
| | በ1 ግዜ አጠቃሎ ከከፋለ | 80 | 70 | 60 |
| | ውል ገብቶ በ6 ወራት **ውስጥ** ከከፈለ | 70 | 60 | 50 |
| | ውል ገብቶ ከ6 ወራት **በላይ** ከፈጀበት | 60 | 50 | 40 |
| 3 | **ባለመክፈሉ** ሃብቱ ተይዞ የመየዣ ማስጠንቀቅያ ከተሰጠ በኋላ | | | |
| | በ1 ወር ውስጥ አጠቃሎመቶ ከከፈለ | 70 | 60 | 50 |
| | ውል ገብቶ በ6 ወራት **ውስጥ** ከከፈለ | 60 | 50 | 40 |
| | ውል ገብቶ ከ6 ወራት **በላይ** ከፈጀበት | 50 | 40 | 30 |
| | | | | |

# በከፊል የሚነሳበት መስፈርት እና መጣኔ...

| ተ.ቁ | ፍሬ፣ወለድና መቀጮ የተከፈለበት ግዜ | የቅጣት አነሳስ ምጣኔ በደረጃ መሰረት | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ዝቅተኛ | መካከለኛ | ከፍተኛ |
| 4 | **ባለ መክፈሉ ሃብቱ ከተያዘ በኋላ ጫረታ ሳይወጣበት** | | | |
| | **በ 1 ግዜ ቀርቦ ከከፈለ** | 60 | 50 | 40 |
| | **ውል ገብቶ በ6 ወራት ውስጥ ከፍሎ ካጠናቀቀ** | 50 | 40 | 30 |
| | **ውል ገብቶ ከ6 ወራት በላይ ከፈጀበት** | 40 | 30 | 20 |
| 5 | **ታክስ ከፋዩ የሚፈለግበትን ታክስ ጫረታ ከወጣበት** በኋላ | | | |
| | በ10 **ቀናት ውስጥ** አጠና**ቆ** ከከፋለ | 50 | 40 | 30 |
| | ውል ገብቶ በ6 ወራት **ውስጥ** ከከፈለ | 40 | 30 | 20 |
| | ውል ገብቶ ከ6 ወራት **በላይ** ከፈጀበት | 30 | 20 | 10 |

## 4.3. አስተዳደራዊ ቅጣት ሙሉ በሙሉ የሚነሳበት አግባብ

- ታክስ ከፋዩ ግዴታውን ለመወጣት ከአቅም በላይ ምክንያት ሲያጋጥመው፤ ድርጅቱ ንግድ ሥራውን የማይቀጥልና የከሰረ መሆኑን ፍ/ቤት ሲያረጋግጥ፤ ከንብረቱ 20% በአደጋ መውደሙን የመንግሥት አካል ካረጋገጠለት፤
- ታክስ ሰብሳቢው የነጋዴውን ሒሳብ ከመመርመሩ በፊት ታክስ ከፋዩ አስተካክሎ ፍሬ፣ ወለድ፣ ቅጣቱን አምኖ በራሱ ከከፈለ፤
- የታክስ ውሳኔ በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ ፍሬ ታክሱን ወለድ እና ጥቃቅን ቅጣቶች ሙሉ በሙሉ ከፍሎ ከጨረሰ፤
- ለቅጣቱ ምክንያት የሆነው ታክስ ሰብሳቢው መ/ቤት የፈጠረው ስህተት ከሆነ።

## 4.4. አስተዳደራዊ ቅጣትን በልዩ ሁኔታ ስለማንሳት

- በኢኮኖሚያዊ፣ አስተዳደራዊ ወይም ማህበራዊ ምክንያቶች የባለሥልጣኑ ሚኒስትር ወይም በሚወክለው ኃላፊ በልዩ ሁኔታ በታክስ ከፋዩ ጥያቄ ወይም ባለሥልጣኑ በራሱ ተነሳሽነት አስተዳደራዊ ቅጣት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል እንዲነሳ ሊያደርግ ይችላል።

## 4.5. በክፍያ ስምምነት ጊዜ ቅጣት አነሳስ

በስምምነቱ መሠረት ፍሬ ታክሱንና ወለዱን ከፍሎ ማጠናቀቁ ሲረጋገጥ መቀጫው እንዲነሳ ይደረጋል።

# 4.6. የማይነሳ አስተዳደራዊ ቅጣት

- የጡረታ መዋጮ እና የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት በወቅቱ ባለመክፈል የተጣለ ቅጣት አይነሳም።
- በዘገየ የታክስ ክፍያ ላይ የሚታሰብ ወለድ የሚነሳ ወይም ቀሪ የሚደረግ አይሆንም።

**ሙከራ አራት**

- አስተዳደራዊ ቅጣት በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ የሚነሳባቸውን እና የማይነሳባቸውን ምክንያቶች ዘርዝሩ?

## ማጠቃለያ

ከታክስ ጋር በተገናኘ የሚፈጠር አለመግባባት፣ የታክስ አስተዳደር እና የወንጀል ቅጣቶች እንዲሁም አስተዳደራዊ ቅጣት አነሳስ በዚህ ሥልጠና የተዳሰሱት ዋና ዋና ርዕሰ ጉዳዮች ናቸው። እነዚህን ርዕሰ ጉዳዮች ወደ ተግባር መቀየር የገቢዎች ሚኒስቴርን እና የግብር ከፋዩን ግንኙነት ሰላማዊ ያደርገዋል።

# ማጣቀሻ

- በፌደራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008
- አስተዳደራዊ ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 9/2011
- የታክስ ወኪልት ፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 4/2011
- የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት አሠራርን መ.ቁ. 171/2013
- የታክስ አስተዳደራዊ ቅጣት አነሳስ መመሪያ ቁጥር 137/2010 እና የመመሪያ ቁጥር 137/2010 መሻሻያ
- Federal Democratic Republic of Ethiopia Federal Tax Administration Proclamation No. 983/2016 Technical Notes


CanStock
© Can Stock Photo - csp15962721
THANK
YOU
alamy stock photo